የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፷፱
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፮ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

17th Year No. 69
ADDIS ABABA 24th May 2011

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፵፩/፪ሺ፫
የጎንደር ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ
የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ .....ገጽ ፭ሺ፰፻፹፯

CONTENTS

Regulation No. 241/2011
Gonder University Re-establishment
Council of Ministers Regulation .....Page 5887

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፩/፪ሺ፫

የጎንደር ዩኒቨርሲቲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፩/፪ሺ፪ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፭፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የጎንደር ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፵፩/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. መቋቋም

፩/ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል።

፪/ የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል ።

፫/ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፭፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲/፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል።

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 241 /2011

COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE RE–ESTABLISHMENT OF THE GONDER UNIVERSITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 5 (1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Gonder University Re-establishment Council of Ministers Regulation No. 241 /2011"

2. Establishment

1/ The Gonder University (hereinafter the "University") is hereby re-established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality.

2/ The University shall be accountable to the Ministry of Education.

3/ The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 210/2011.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazeta P.O. Box 80,001

፫. ዋና ግቢ

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በጎንደር ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

፬. የተሻረ ደንብ

የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፩፻፲፪/፲፱፻፺፯ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

፭. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

3. **Main Campus**

The University shall have its main campus at Gonder and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services .

4. **Repealed Regulation**

The Gonder University Establishment Council of Ministers Regulation No. 112/2004 is hereby repealed.

5. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 24 th day of May , 2011.

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፮ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት